መልእክት አሥራ-አንድ

## ዳዊት እና አቢግያ
## ተዋጊውን ክርስቶስን እና ተዋጊዋን ቤተ ክርስቲያን በምሳሌ ማሳየታቸው

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 1 ሳሙ. 25፡2-42፤ ኤፌ. 5፡25-27፤ 6፡10-13፤
ራእ. 19፡7-9፣ 11-21፤ ዕብ. 6፡19፤ 10፡19-20፤ 13፡13

**I. አንደኛ ሳሙኤል 25፡1-44 ዳዊት ከናባል ጋር የነበረው እሰጥአገባና እና ከአቢግያ ጋር የነበረው ልውውጥ ዘገባ ነው፦**

ሀ. በዚህ ምዕራፍ ዳዊትን ያስታገሰችበትን የአቢግያን ጥበብ እናያለን—ቁ. 23-31።

ለ. ዳዊት ለአቢግያ ይግባኝ እርሱን እንድትገናኘው የላካትን ያህዌን በመባረክ እና ደም ወደማፍሰስ ከመግባት እና በራሱ እጅ በቀል ከማድረግ የከለከለችውን እርሷንም በመባረክ መለሰ—ቁ. 32-35።

ሐ. የአቢግያ ጥበብ እና ውበት ዳዊትን ማረከው፣ ከናባልም ሞት በኋላ ሚስቱ አድርጎ ወሰዳት፣ እርሷም በውጊያ አምሳያው ሆነች—ቁ. 36-44።

**II. ዳዊት በመከራው መካከል ተዋጊውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል—ቁ. 28፦**

ሀ. ዳዊት ጌታ ኢየሱስን እንደ ሰው ከትንሣኤው በፊት በምድር ላይ በነበረው መከራው በምሳሌ ያሳያል፤ የዳዊት መከራ ያለአግባብ የሚይዙ ጠላቶቹን ለማሸነፍ እና ለእግዚአብሔር ግንባታ መቆሚያ ስፍራ የሆነችውን መልካሚቱን ምድር ለማግኘት ነበር—መዝ. 69፡1-9።

ለ. ዳዊት በእግዚአብሔር ተቀባይነት ማግኘቱ በፍልስጤማውያን ላይ በነበረው ተደጋጋሚ ድሎች ታይቷል፤ ስለዚህ፣ የተዋጊው ክርስቶስ ምሳሌ ነው—2 ሳሙ. 5፡17-25።

ሐ. ያህዌ ውጊያውን ለእኛ የሚዋጋ እና ጠላቶቻችንን ሁሉ የሚያሸንፍ ተዋጊ ስለሆነ፣ እርሱ ማሸነፋችን፣ ድላችን ነው—ዘጸ. 17፡8-16።

መ. መዝሙር 110፡5-6 ንጉሥ እና ካህን ከመሆን በተጨማሪ፣ ክርስቶስ ተዋጊ መሆኑን ይገልጣል፦

1. በቁጣው ቀን ተመልሶ ሲመጣ፣ ክርስቶስ አሕዛብን ሁሉ ድል-የሚነሣ፣ የነገሥታትን እና የጠላቶቹን ራስ የሚቀጠቅጥ፣ እና በሚቃወሙት ሁሉ ላይ ፍርድን የሚያስፈጽም ታላቁ ድል-ነሺ ይሆናል—ቁ. 1-2፣ 5-6።
2. በራእይ 19፡11-14 መሠረት፣ ተመልሶ በመምጣቱ ክርስቶስ ተዋጊው ይሆናል፦
   ሀ. ጌታ ከክርስቶስ ተቃዋሚው እና ከአሕዛብ ሠራዊት ጋር ብቻውን አይዋጋም።
   ለ. ክርስቶስ ሠራዊቱ ከሆነችው ከሙሽራው ጋር ይመጣል፣ ከእርሷም ጋር ሆኖ ከክርስቶስ ተቃዋሚው እና ከሠራዊቱ ጋር ይዋጋል—ቁ. 7-9።

ሠ. ተዋጊው ክርስቶስ ድል ነሺው ክርስቶስ ነው—ዮሐ. 12፡31፤ ኤፌ. 4፡8፤ ዕብ. 2፡14፦

1. በምድር በነበረው አገልግሎቱ ድል ነሺው ክርስቶስ ዲያቢሎስን አሸንፎታል፣ ሥራውንም አፍርሶበታል—ማቴ. 4፡1-11፤ 1 ዮሐ. 3፡8።
2. በመሰቀሉ ድል ነሺው ክርስቶስ የዚህን ዓለም ገዢ ጥሎታል፣ ዲያቢሎስን ደምስሶታል፣ አለቆችን እና ሥልጣናትን ገፏቸዋል፣ ሞትንም ሽሯል—ዮሐ. 12፡31፤ ማቴ. 27፡51፤ ዕብ. 2፡14፤ ቆላ. 2፡15፤ 2 ጢሞ. 1፡10።
3. የድል ነሺው ክርስቶስ ትንሣኤ በሞት ላይ አሸናፊ መሆኑን ያውጃል—2፡8።
4. በዕርገቱ ድል ነሺው ክርስቶስ "ምርኮን ማረከ"፤ ያለአግባብ ከሚይዘው ከሰይጣን እጅ ፈትቶ በአጽናፍ-ዓለም ወዳለ ወደ ከፍተኛው ስፍራ አምጥቶናል—ኤፌ. 2፡6፤ 4፡8።
5. ድል ነሺው ክርስቶስ ከሠራዊቱ ጋር የክርስቶስ ተቃዋሚውን፣ ከበታቹ ያሉትን ነገሥታት እና ሠራዊታቸውን በአርማጌዶን ለመዋጋት እንደ ተዋጊው ጀነራል፣ እንደ ተዋጊው ይመጣል—ራእ. 19፡11-21።

**III. አቢግያ በመከራዎቿ መካከል ተዋጊዋን ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ታሳያለች—1 ሳሙ. 25፡2-42፦**

ሀ. ከ 1ኛ ሳሙኤል 25 ጀምሮ፣ አቢግያ ሁልጊዜ ከተዋጊው ዳዊት ጎን ነበረች፣ በውጊያዎቹ ውስጥም ተከተለችው—ቁ. 40-42፦

1. አቢግያ ከዳዊት ጋር መጋባቷ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሠራዊት ለጦርነት መመልመሏን በምሳሌ ያሳያል—ኤፌ. 6፡10-20።
2. አቢግያ በመከራዎች መካከል ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትዋጋውን ተዋጊዋን ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ታሳያለች—ራእ. 1፡9፤ 11፡15፤ 12፡10።

ለ. የአቢግያ ምሳሌ በመከራዎቹ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን እንደሚያስፈልገን ያሳያል—ፊልጵ. 3፡10፤ ቆላ. 1፡24፤ ራእ. 1፡9፦

1. የክርስቶስ መከራዎች በሁለት ምድቦች ናቸው፦ ቤዛነትን ለመፈጸም በራሱ በክርስቶስ የተፈጸሙት እና ቤተ ክርስቲያንን ለማፍራት እና ለመገንባት በሐዋርያት እና በአማኞች መሞላት የሚያስፈልጋቸው ናቸው—ቆላ. 1፡24።
2. ጳውሎስ የክርስቶስን መከራዎች ከእግዚአብሔር መጋቢነት ጋር አገናኝቶ መጥቀሱ የሚያመለክተው መጋቢነት መከናወን የሚችለው በመከራ በኩል ብቻ መሆኑን ነው—ቁ. 25፦
   ሀ. በእግዚአብሔር መጋቢነት ውስጥ ለመሳተፍ ከፈለግን፣ መከራ ለመቀበል መዘጋጀት አለብን—ራእ. 1፡9፤ 2 ቆሮ. 1፡3-6።
   ለ. በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ወይም [በቃሉ] አገልግሎት የሚሳተፉ ሁሉ የመጋቢን መከራዎች ለመካፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው፤ ይህ ማለት መጋቢነታችንን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን አለብን—4፡10-12፤ ዮሐ. 12፡24-26።

ሐ. የአቢግያ ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ኢየሱስ ጋር በመንፈሳዊ ውጊያ ያላትን ተሳትፎ ያሳያል—ኤፌ. 6፡10-20፦

1. ቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አምሳያ፣ እንደ ሙሽራው በኤፌሶን 5፡25-27 ተገልጣለች፣ ይህችም አምሳያ በኤፌሶን 6፡10-13 ወታደር፣ ተዋጊ ትሆናለች፦
   ሀ. ኤፌሶን 5 እና 6 በራእይ 19 ይፈጸማሉ።
   ለ. የድል ነሺዎቹ ጥቅል ድምር የክርስቶስ አምሳያ ለመሆን ሙሽራይቱ ይሆናል (ቁ. 7-9)፣ ይህችም አምሳያ በአርማጌዶን የክርስቶስ ተቃዋሚውን ለማሸነፍ የክርስቶስ ሠራዊት ትሆናለች (ቁ. 11-21)።
2. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ መፈጸም እና የልቡ መሻት መርካት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጠላትም መሸነፍ አለበት፤ ለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን ተዋጊ መሆን አለባት—ኤፌ. 1፡11፤ 3፡9-11፤ 6፡10-12።
3. መንፈሳዊ ውጊያ የግድ አስፈላጊ የሆነው የሰይጣን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተጻራሪ ስለተቀመጠ ነው—ማቴ. 6፡10፤ 7፡21፤ ኢሳ. 14፡12-14፦
   ሀ. መንፈሳዊ ውጊያ ምንጩ በመለኮታዊው ፈቃድ እና በሰይጣናዊው ፈቃድ መካከል ያለ ግጭት ነው።
   ለ. እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ ውጊያችን ሰይጣናዊውን ፈቃድ ለማስገዛት እና የእግዚአብሔርን ጠላት ለማሸነፍ ነው—ራእ. 12፡11።
4. ሰይጣን የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን፣ እርሱን እና መንግሥቱን የምትዋጋውን ብዙዎች የተካተቱባትን ተዋጊ ይፈራታል—ማቴ. 6፡10፤ ኤፌ. 6፡10-20።
5. ክርስቶስ ውጊያውን ከእግዚአብሔር ጠላት ጋር ለዓመታት ስትዋጋ የነበረችውን እርሷን ያገባል—ራእ. 19፡7-9፣ 11-16።
6. የክርስቶስን ሙሽራ የሚያቀናብሩት ድል ነሺዎቹ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ሁሉ ጋር ውጊያውን ይዋጋሉ፣ የእግዚአብሔርንም መንግሥት ለማምጣት ያሸንፏቸዋል—2፡7፣ 11፣ 17፣ 26፤ 3፡5፣ 12፣ 21፤ 11፡15፤ 12፡10።

## IV. የአቢግያ ምሳሌ ነቀፌታውን እየተሸከመ ከሰፈሩ ውጭ ወደ ኢየሱስ የሚወጣን አማኝ ያሳያል—ዕብ. 13፡13፦

ሀ. የክርስትና ሕይወታችን ሁለት ገጽታዎች አሉት—ውስጣዊ ገጽታ እና ውጫዊ ገጽታ—ዕብ. 6፡19-20፤ 13፡13፦

1. ውስጣዊው ገጽታ በሱላማጢስ ተመስሏል፣ ውጫዊው ገጽታ ደግሞ በአቢግያ ተመስሏል—መኃ. 6፡4፣ 10፣ 13፤ ዕብ. 13፡13።
2. በአንድ በኩል፣ በመጋረጃው ውስጥ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነን፤ በሌላ በኩል፣ ከከተማው፣ ከሰፈሩ ውጪ በሰዎች ፊት ነን—ዕብ. 6፡19-20፤ 13፡13፦
   ሀ. በውስጥ፣ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ እንደሰተዋለን፣ በውጪ፣ ኢየሱስን እንከተለዋለን—6፡19፤ 13፡13።
   ለ. ጌታን በውስጠኛው እልፍኝ፣ በቅድስተ ቅዱሳን፣ በምሥጢራዊው ስፍራ ውስጥ ስንነካው፣ ከሱላማጢስ ጋር ልንመሳሰል እንችላለን—10፡19-20፤ መኃ. 1፡4፤ 4፡10፤ 6፡13።
   ሐ. በውጫዊ ኑሯችን ለጌታ ስንመሰክር እና ለጌታ ስንሠራ፣ በምድረ በዳ ከዳዊት ጋር ከምትቅበዘበዘው ከአቢግያ ጋር ልንመሳሰል እንችላለን—1 ሳሙ. 25፡40-42።

ለ. እነዚህን ሁለት ገጽታዎች በየቀኑ መለማመድ እንችላለን—ዕብ. 6፡19-20፤ 10፡19-20፤ 13፡13፦

1. በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እየኖርን እና ከሞት የተነሣውን እና የከበረውን ክርስቶስ እየተደሰትን እንደ ሱላማጢስ በመጋረጃው ውስጥ ነን፣ በዓለም እየኖርን እና የተዋረደውን ኢየሱስን እየተከተልን እንደ አቢግያ ከሰፈሩ ውጪ ነን—6፡19-20፤ 13፡13።
2. እንደ ሱላማጢስ እና ሰለሞን፣ ከዝሆን ጥርስ በተሠሩ ቤተ መንግሥቶች ውስጥ እንቆያለን፣ ከጌታም ጋር በውስጥ ኅብረት እናደርጋለን፣ እንደ አቢግያ፣ ለጦርነት እና መከራ ለመቀበል ዳዊትን በመከተል በውጪ እንኖራለን እንሠራማለን—መዝ. 45፡8፤ 1 ሳሙ. 25፡40-42።
3. በውስጣችን ያለው እርሱ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ነው፣ በውጪ ያለው እርሱ ደግሞ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው—ራእ. 1፡17-18፤ ማቴ. 2፡23።
4. በውስጥ፣ በምሥጢር ስፍራ የሱላማጢሷ ድሰታ አለን፣ በውጪ፣ የአቢግያ የገሃድ ኑሮ አለን።

ሐ. በክርስቶስ የሚያምን አማኝ ከመጋረጃው ውስጥ፣ ከውስጠኛው የኅብረት እልፍኝ ሲወጣ፣ የመስቀሉን መንገድ መውሰድ እና መከራ የሚቀበለውን ኢየሱስን መከተል ይችላል—ዕብ. 6፡19፤ 10፡19-20፤ 13፡13፦

1. በመጋረጃው ውስጥ የሚገቡ ብቻ ከሰፈሩ ውጪ ወደ ኢየሱስ መሄድ እና ነቀፌታውን መሸከም ይችላሉ—6፡19፤ 10፡19-20፤ 13፡13።
2. መከራ የሚቀበለውን ኢየሱስን እንድንከተል የሚመራን ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ነው—ቁ. 13።
3. ጌታ ኢየሱስ የመስቀሉን መንገድ ተራምዶ ወደ ትንሣኤ ውስጥ ገብቷል፣ አሁን የመስቀሉን መንገድ እንድንወስድ እና ነቀፌታውን ተሸክመን ከሰፈሩ ውጪ እንድንከተለው እኛን፣ አቢግያዎቹን እየመራን ነው—ቁ. 13።

*© 2021 Living Stream Ministry*